*ምዕራፍ 119*

# በትህትና ጀምር በትህትና ጨርስ

ብዙ መሪዎች በጭምትነት ይጀምሩና በራሳቸውና በውጤቶቻቸው በኩራት ተሞልተው ይጨርሳሉ።

ትምክህት ውድቀትን ትቀድማለች እናም ይህ ራስን የማውደም ቁልፍ ነው በብዙ መሪዎች ሕይወት ጉልቶ የሚታየው። በሕይወት ከኖሩት ታላላቅ መሪዎች ሁለቱ በጭምትነት ጀምረው በጭምትነት ጨርሰዋል። ከእነርሱ ምሳሌነት ተማር።

## ኢየሱስ አገልግሎቱን በጭምትነት ጀምሮ በጭምትነት ነው የጨረሰው

1. ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በበረት ውስጥ ነው የጀመረው

የበኵር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።

ሉቃስ 2፡7

2. ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በመስቀል ላይ ነው ያበቃው።

ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።

ሉቃስ 23፡46

## የጳውሎስ ጭምትነት አራት ደረጃዎች

ጳውሎስ በአራት ተከታታይ ጭምትነቶች አልፏል።

1. ከማናቸውም ሐዋሪያት እንደማያንስ ተናግሮ ነበር።

በመመካቴ ሞኝ ሆኜአለሁ፤ እናንተ ግድ አላችሁኝ፤ እናንተ እኔን ልታመሰግኑ ይገባ ነበርና። እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና።
2ኛ ቆሮንቶስ 12፡11

2. እያደገ በመጣ ቁጥር ከሐዋርያቱ ታናሽ እንደሆነ ተሰማው

እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤

1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9

3. ከጥቂት ተጨማሪ ጊዜ በኋላ ጳውሎስ የቅዱሳን ሁሉ ታናሽ እንደሆነ አሰበ።

**ፍሊጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ አገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ፤**

ኤፌሶን 3፡8-9

እንደምታየው፣ ጳውሎስ በአገልግሎት ይበልጥ ልምድ እያገኘ ሲሄድ ስለራሱ ያለው ግምት እያነሰ ሄደ። በጌታ ከፍ እያልክ በሄድክ ቁጥር ምን ያህል እምብዛም የማያስፈልግ መሆንህን በይበልጥ ትገነዘባለህ። በሥራ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ የአንተ የግል ጥረቶች እንዳልሆኑ ትደርስበታለህ።

4. በአገልግሎቱ ፍፃሜ ላይ ጳውሎስ የአመፀኞች ዋና እንደሆነ ወሰነ።

**ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤**

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15

ጳውሎስ የሆነ አሳዛኝ ሐጢያት ሰለስራ አልነበረም። ከብስለት ጋር የእርሱና በእርግጥም የሰው ሁሉ ኃጢአት ማንነት መረዳት አብሮ መጣ።

## ያከናወንካቸው ነገሮች እንዲያስመኩህ አትፍቀድ

ውጤቶችህ ለለራስህ ያለህን አስተሳሰብ እንዲቀይሩ አትፍቀድ። ናቡከደነፆር በቤተመንግሥቱ በገነት ላይ ሲመላለስ አስቃቂ ስህተት ሰራ። *በራሱ ብርታት ታላላቅ ነገሮችን እንዳከናወነ አሰበ።*

**ከአሥራ ሁለት ወር በኋላ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሰገነት ላይ ይመላለስ ነበር። ንጉሡም። ይህች እኔ በጕልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን? ብሎ ተናገረ።ቃሉም ገና በንጉሡ አፍ ሳለ ድምፅ ከሰማይ ወደቀና። ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ። መንግሥት ከአንተ ዘንድ አለፈች ተብሎ ለአንተ ተነግሮአል**

ዳንኤል 4፡29-31

ናቡከደነፆር ስለራሱ የተጋነነ ግምት ሲያዳብር እግዚአብሔር ቀጣው። መሪ ከሆንክ ስለ ከንውኖችህ የማይረባ ቃላትን አትናገር። የፖለቲካ መሪዎች በሥልጣን ላይ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ የማይረባ ንግግሮችን ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አንዳንድ መሪዎች ጭራሽ ለዘለዓለም የሚኖሩ ይመስላቸዋል። ነገር ግን በጣመ በቀላሉ ልትነሳ ትችላለህ። አባትህንና ቅድመ አያቶችህን ለዘለዓለም ኖረው እንደሆነ ጠይቃቸው።

> አባቶቻችሁ ወዴት ናቸው? ነቢያትስ ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን?
>
> ዘካርያስ 1፥5

## በሌሎች መሪዎች ላይ አትሳቅ

ሥጋ ለባሽ ብቻ ስለሆንክ ስለራስህ ጭምት የሆነ አስተሳሰብ ይኑርህ። በችግር ውስጥ ባለ ሌላ መሪ ላይ አትሳቅ። ፈራጅ መሪዎች ለውድቀት ያዘነበሉ መሆናቸውን ታሪክ አስተምሮናል። ሌሎች መሪዎች በኃጢአት ውስጥ ሲወድቁ አታፌዝ። ሳዖል በጦርነት ሲገደል የዳዊት ምላሽ ምን ነበር? "የእጁን አገኘ" በፍጹም አላለም! ከሚያዝኑ ጋር አዘን አብረዛቸው ፀልይ። በሌላ ታላቅ መሪ ውድቀት የሐዘን እንጉርጉሮ ያሰማን የአንድ ታላቅ መሪን ቃላት አስተውል።

> ማልደው ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ፥ ተመልሰውም ወደ አርማቴም ወደ ቤታቸው መጡ። ሕልቃናም ሚስቱን ሐናን እወቃት እግዚአብሔርም አሰባት የመፅነስዋም ወራት ካለፈ በኋላ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች እርስዋም፦ ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ ስትል ለሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው።ሰውዮውም ሕልቃና ከቤተ ሰቡ ሁሉ ጋር የዓመቱን መሥዋዕትና ስእለቱን ለእግዚአብሔር ያቀርብ ዘንድ ወጣ።
>
> 1ኛ ሳሙኤል 1፥19-21

## ምዕራፍ 120

# ሰዎችን እንዲያምኑብህ አሳምናቸው

ናትናኤልም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው። ፊልጶስ። መጥተህ እይ አለው።ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ። ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ።ናትናኤልም። ከወዴት ታውቀኛለህ? አለው። ኢየሱስም መለሰ፦ ፊልጶስ ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች ሳለህ፥ አየሁህ አለው።

ዮሐንስ ወንጌል 1:47-49

ኢየሱስ ናትናኤልን እንዲያምንበት አድርጓል። ናትናኤል ኢየሱስ ጥሩ ሰው እንደሆነና ሊከተለው እንደሚገባ የግል የሆነ እምነት ነበረው። ማንም ሰው በአንተ ካላመነብህ ማንም ሀሳቦችህን ሊከተል አይችልም። መሪዎች ግልፅ መሆን ካለባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰዎች በግል እንዲያውቋቸው እድሉን እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። አንዳንድ ጊዜ ስለግል ሕይወታቸው ምንም የማይናገሩን ሰባኪዎች ስመለከት ይገርመኛል። የማስጡት ምሳሌ ወይም የሚያካፍሉት ምስክርነት ስለሌላቸው ይሆን? ውድ ጓደኛዬ የምትመራቸው ሰዎች እንደ አንድ ግለሰብ በአንተ ላይ እምነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ለእነርሱ ክፍት ካልሆንክ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሰዎች በልብህ ውስጥ ያለውን የሚያውቁት በቃሎችህ ነው።

እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።

ማቴዎስ 12:34

ሰዎች በአንተ ልብ ውስጥ ካሉ ነገሮች ጋር መዛመድ ከቻሉ እንዲሄዱ ወደ ምትፈልገው ሥፍራ ሁሉ በፍጥነት ይሄዳሉ። የተጻፈላቸውን ንግግሮች በሚያነቡ ሰዎች አልገረምም። ከልቡ ሲናገር ካልሰማሁት በስተቀር ስለ ሰውየው ብዙ ላውቅ አልችልም። ወሳኙ ልብ ነው። ሰዎች ወኔህን፣ ተነሳሽነትህንና ራእይህን ሊሰሙት ከተቻለ መምራት ቀላል ይሆናል። ለምንም ነገር ወኔ ከሌለህ ወይም የሆነን ነገር ለማከናወን ተነሳሽነት ከሌለህ መሪ አይደለህም።

ወኔ እና የፀና እምነት እንዲኖርህ ጸልይ። ስለ ውክልና፣ ስልጣንና ሥራ አስኪያጅነት የተወሰኑ ደንቦችን መማር መሪ አያደርጉህም። ያ ከልብ የሆነውን መሪነትህን ማሳደግ ብቻ ነው የሚችለው። ብዙ

የአመራር ትምህርት ቤቶችና መጻሕፍት እያሉን እንዲህ ጥቂት መሪዎች የመኖራቸው ምክንያት መሪነት ከልብ በመሆኑ ነው። ሰዎች ከልባቸው ካላመኑብህ በስተቀር ከልባቸው አይከተሉህም።

## ሰዎች እንዲያምኑብህ የማድረጊያ ሰባት መንገዶች

### 1. ስለ ግል ሕይወትህ ግልፅ ሁን

ሕይወትህን የከበቡ ብዙ እንቆቅልሾች ካሉ ሰዎች በተፈጥሮ ወደ አንተ አይሳቡም።

### 2. ስለ ችግሮችህ እውነተኛ ሁን

መሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ሰው ችግሮች አሉበት። ሰዎች እውነተኛ ብለው በሚያስቧቸው መሪዎች ዙሪያ ይሰበሰባሉ። እውነተኛ መሪ ሁሉም ያለበትን ዓይነት ችግሮች አሉበት ነገር ግን የሚወጣቸው ሰው ነው። የትዳር ችግሮች ካሉብህ በግልጥ ተናገራቸውና እግዚአብሔር አንተንና ባለቤትህን እንድትወጡት እንደሚረዳችሁ ለሌሎች አካፍል።

### 3. ከልብህ ስበክ

በፍጹም ስብከትን ለሕዝቡ አታንብብ።አንድ ጊዜ አንድ ዓለማዊ የአገር ገዢ በቁጣ ሲማረር ሰማሁ። እንዲህ "ንግግሮችን ሳደርግ ከልቤ እናገራለሁ! ከእግዚአብሔር የሚለማ ቄስ ለምን መልእክቱን ለእኔ ማንበብ አስፈለገው?" ስብከቶችን ስታነብ አድማጮችህ እውነተኛነትህን ሊጠራጠሩ ይችላሉ። የተፃፈ ነገር ሁሉ በጥንቃቄ የታሰበ ነው። መስማት የምንፈልገው በልብህ ያለውን ነው።

> እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤
>
> ማቴዎስ 12፡36

### 4. ከእግዚአብሔር ጋር ያሉህን ልምምዶች አካፍል።

ከእግዚአብሔር ጋር የግል ልምምድ መኖሩ ለመሪ ተዓማኒነትንና ሥልጣንን ይሰጠዋል። ሲጀመርም የክርስትናህ መሪነት የተመሠረተው አንተ ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ ነው። የመልአክ ወይም የኢየሱስ ጉብኝት ደርሶህ ከሆነ ለሌሎች አካፍለው፤ አስፈሪውን የእግዚአብሔር መገኘት ያወርዳል።

## 5. እግዚአብሔር የነገርህን ለሰዎች ንገራቸው

እግዚአብሔር ከተናገርህ አካፍል፡፡ ለሰዎች እግዚአብሔር እንደተናገርህ መናገር መቻል ታላቅ የእምነት እርምጃ ነው፡፡ ጌታ በግል አንተን እንደወከለህ ያሳያል፡፡ ሰዎች እግዚአብሔር መከተል ይፈልጋሉ፤ ስለዚህ አንተ ከእግዚአብሔር ከሰማህ አንተን መከተል ይፈልጋሉ፡፡

## 6. ስራእይህ መሥዋዕትነትን አድርግ

ሰዎች ለምታምነው ነገር የምታደርቻውን መሥዋዕትነቶች ማየት ይችላሉ፡፡ መሥዋዕትነትህ ከመቶ ስብከቶች ይልቅ ጮኾ ይናገራል፡፡ እኔ የሕክምና ሙያዬን ስአገልግሎቱ ሰውቻለሁ፡፡ ያ አንድ ተግባር ከምንም ነገር የበለጠ ተአማኒነት ሰጥቶኛል፡፡ ሰዎች መሥዋዕትነትህን ሲያዩ በአንተ ያምናሉ፡፡

## 7. የምትጸልይ ሁን፡፡ ጸሎት መንፈሳዊ ሥልጣንን ያስገኛል፡፡ ሥልጣን ያ "የእግዚአብሔርን ሰው የሚከብበው በቀላሉ የማይገለጽ፣ የማይታይ፣ የሚስብ መንፈስ" ነው፡፡

ሥልጣን ለእግዚአብሔር ካለህ ቅርበት የሚመነጭ ነው፡፡ አንድን ሰው በቀረብከው ቁጥር ስለ እርሱ የበለጠ በድፍረት መናገር ትችላለህ፡፡ ሰዎች በጸሎት ሕይወትህ ምክንያት በአንተ ያምናሉ፡፡ ይህ ብዙ ጸሎት አሰባ ሰዎች የማያውቁት ምስጢር ነው፡፡ ሰዎች ጸሎት የለሽ መሪዎችን አይከተሉም፡፡ የግል ጸሎትህ ሰዎች በአንተ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል፡፡

# የምታናግረውን ሰው እንደማንነቱ አይተህ ብዙ ተናገር ወይም ምንም አትናገር

መሪ የሚያናግረውን ሰው ማንነት ላይ ተመስርቶ ብዙ ወይም ጥቂት መናገርን መማር አለበት። ኢየሱስ ክርስቶስ በጉዑ አድማጮች ተከቦ ሳለ ለሰዓታት ይናገር ነበር። ሰዎች ለመስማትና ለመፈወስ ኪሎሜትሮችን አቋርጠው ይመጡ ነበር። ሰዎች ተመልሰው ወደ ቤታቸው መሄድ እስከማይችሉ ድረስ ለሰዓታት ይሰብክ ነበር።

በደጅ ያለው ስፍራም እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም ይነግራቸው ነበር።

ማርቆስ 2፡2

ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ ሲያስጠብቡት ሳሉ፥ እርሱ ራሱ በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር፤

ሉቃስ 5፡1

ኢየሱስ በሚጠሉትና በሚንቁት ሰዎች መካከል ሲሆን ምንም አልተናገረም። ጊዜ ሁሉን እንደሚፈታ (እንደሚናገር) ያውቅ ነበር።

## ኢየሱስ ሊያናግራቸው ያልፈለገ ሶስት ሰዎች

1. ኢየሱስ ለሃይማኖት መሪዎች የሚለው አልነበረውም።

ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ። አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው።እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም። ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና። የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው።

ማርቆስ 14፡60-61

2. ኢየሱስ ለገዥው ለጲላጦስ የሚለው አልነበረውም።

ጲላጦስም። አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም፦ አንተ አልህ ብሎ መለሰለት።የካህናት አለቆችም ብዙ ያሳጡት ነበር፤ እርሱ ግን ምንም አልመለሰም። ጲላጦስም ደግሞ። አንዳች አትመልስምን? እነሆ፥ በስንት ነገር ያሳጡሃል ብሎ ጠየቀው።ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ ምንም አልመለሰም።

ማርቆስ 15፡2-5

### 3. ኢየሱስ ለሄሮድስ የሚለው አልነበረውም

> ፋሲካንም ሊያርዱበት የሚገባው የቂጣ በዓል ደረሰ፤ጴጥሮስንና ዮሐንስንም። ፋሲካን እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን ብሎ ላካቸው።እርሱም፦ ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ? አሉት።እርሱም አላቸው። እነሆ፥ ወደ ከተማ ስትገቡ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ ወደ ሚገባበት ቤት ተከተሉት፤
>
> ሉቃስ 23፡7-10

እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የሚጠሉት ነበሩ፤ እርሱም ያውቀው ነበረ። እርሱ የሚናገረው ምንም ነገር እስተሳሰባቸውን እንደማይቀይር ያውቅ ነበር። የንግግር ባለሙያን ምክር ከመከተል የኢየሱስን ምሳሌነት መከተል እመርጣለሁ። ብዙ ጉዳዮችን ለእግዚአብሔርና ለጊዜ ትቻለሁ። ለሁሉም ክስ እርሱ የተሻለ መልስ አለው። ኢየሱስ በኃይል ቢከሰስም ለክሶቹ አስተያየትም ሆነ መልስ መስጠት አለፈለገም። ኢየሱስ መናገር ስለማይችል አልነበረም። በተራራው ላይ እንዴት እንደሰበከ እናያለን። በባሕር ዳር እንዴት እንዳስተማረ እናያለን። ከስብከቱ በኋላ ሰዎችን መመገብ እስኪኖርበት ድረስ እንዴት ረጅም ሰዓት እንደሰበከ እናያለን።

ብዙ መጋቢዎች ቃለመጠይቆችና ውይይቶች ላይ መገኘት እንዳለባቸው ይሰማቸዋል። ስማቸውን የማጥራትና ገጽታቸውን የማሻሻል ግዴታ ያለባቸው ይመስላቸዋል። ልብ በል መጋቢዎች ጋዜጠኞችን ማናገርም ሆነ ቃለ መጠይቅ ማድረግ የለባቸውም እያልኩ አይደለም። የምለው ምንም ቢሆን ሀሳባቸውን የማይለውጡ፣ ጥላቻን የተሞሉና ተቃዋሚ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎችን ለማነጋገር ኢየሱስ አልተጨናነቀም ነው። ሁሉም አገልጋይ የኢየሱስ ክርስቶስን አርአያነት እንዲከተል እመክራለሁ።

## መጋቢዎች ጋዜጠኞችን ማነጋገር የማይገደዱበት ሶስት ምክንያት

### 1. መገናኛ ብዙሃኑ የወንጌልን አገልጋይ የመገንባትም የማፍረስም ኃይል የላቸውም።

ብዙ የመገናኛ ብዙሃን ሰዎች ይህ ኃይል እንዳላቸው አድርገው እንደሚያስቡ አውቃለሁ። ጲላጦስም ኢየሱስን ለማጥፋትም ሆነ ለማጽናት ኃይል እንዳለው አስቦ ነበር።

> ስለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።
>
> ዮሐንስ 19፡10

## ኢየሱስ ግን አረመው

> ኢየሱስም መልሶ፡- ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።
>
> ዮሐንስ 19፡11

በተመሳሳይ መንገድ ብዙ ጋዜጠኞች ከፈለጉ የእግዚአብሔርን ሰው ወይም አንዲትን ቤተክርስቲያን የማውደም ጉልበት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። እግዚአብሔር ካልፈቀደ በስተቀር ማንም ምንም የማድረግ ሥልጣን የለውም። ኢየሱስ በእነዚያ መልስ ባልሰጠባቸው ክሶች ምክንያት አገልግሎቱ እየፈረሰ እንደሆነ ቢያስብ ኖሮ መልስ ይሰጥ ነበር። ይህንን ምስጢር ተማር፣ ማንምኛውም ሰብዓዊ ፍጡር እግዚአብሔር የገነባውን ሊያውድም አይችልም። እነዚያ ክሶች ወደፊት በእነዚያ ሐሰተኞች ላይ ለሚፈርደው ፍርድ እንደ መነሻ ሆነው ብቻ ነው የሚያገለግሉት። የሆነን ነገር ያወደሙ ሊመስል ይችላል፤ እውነታው ግን የእግዚአብሔርን የእጅ ሥራ ማንም ሊያወድም አይችልም።

2. መጋቢዎች ቃሎቻቸውን በእውነት ለሚያደንቁት ለጉባዔዎቻቸው መቆጠብ አለባቸው።

ለአገልግሎት ተገቢው መሰባሰብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንጂ ለሚያጣጥሉ ለሚንቁ የ"ቶክ ሾው" አዘጋጆች እንዳልሆነ መጋቢዎች ሊያውቁት የሚገባ ነው ። ከጅምሩ የሚያደሉና ጥላቻን የተሞሉ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች ኢየሱስን ሲጠይቁት የሚናገረው ምንም አዲስ ነገር እንደሌለው አስረዳቸው። ማለት የሚገባውን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ብሎ ነበር።

> ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው። ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኩራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ በስውርም ምንም አልተናገርሁም።ስለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው።
>
> ዮሐንስ 18፡19-21

እንዲህ ዓይነቱ መልስ ብዙ ዘጋቢዎችን ያበሳጫል። በእርግጥ በዚያ ቀን የነበሩትን ሰዎች አንገብግቧቸዋል።

> ይህንም ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ። ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው።ኢየሱስም መልሶ፡- ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፤ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? አለው።
>
> ዮሐንስ 18፡22፣23

## 3. መጋቢ ራሱን ለሰዎች ትክክል እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ የለበትም።

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለህ ከሆንክ ለማህበረሰቡ አስደሳች ሆነህ መታየተ አያስፈልግህም። ራስህን በሰዎች ፊት ተቀባይነት እንዲኖርህ ጥረቶችን ማድረግ እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑ ይችላሉ።

> **እንዲህም አላቸው፡- ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩስት ነውና።**
>
> **ሉቃስ 16፡15**

### ምዕራፍ 122

# የደረጃ የማዕረግን መርህ ተቀበል

እንደ ኃያላን ይሮጣሉ፥ እንደ ሰልፈኞችም በቅጥሩ ላይ ይወጣሉ እያንዳንዱም በመንገዱ ላይ ይራመዳል፥ ከእርምጃቸውም አያፈገፍጉም።

ኢዮኤል 2፡7

## ስለ ማዕረግ እያንዳንዱ መሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ አስር ነገሮች

1. ሁላችንም አንድ ዓይነት እንድንሆን አልተፈጠርንም:: ማዕረግ መስጠት ለዚህ እውነታ ዕውቅና መስጠት ነው::

አ

ንዳንድ የፖለቲካ ዘይቤዎች ሁሉንም ሰው አንድ ዓይነት ለማድረግ ሞክረዋል:: እግዚአብሔር እኩል እንድንሆን አልፈጠረንም:: መሪ በነገሮች ድልድል ውስጥ ሥፍራ እንዳለው የሚረዳ ሰው ነው::

2. ማዕረግህ የተግባርህን ደረጃ ያሳያል

ምን ያህል ከፍ ወይም ዝቅ እንዳልክ ይነግርሃል:: ማዕረግህ በእግዚአብሔር ወይም በሰው የበላዮችህ ሊሰየም ይችላል::

3. ማዕረግ ሰውንና ድርጅትን ማጭታታትን ያስቀራል::

4. ማዕረግ ከዚህ በላይ ምን ያህል ከፍ ብለህ ልትሄድ እንደምትችል ያሳይሃል::

ከእኔ ይልቅ በአገልግሎታቸው የበለጠ ዕድገት ስላላቸው ሰዎች አውቃለሁ:: ጌታ በሚያደርገው ነገር ከእነርሱ ጋር ደስ እሰኛለሁ:: ሊኖር በሚችለው ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዳልሆንኩ አውቃለሁ:: ከእኔ የሚቀድሙትን አከብራለሁ::

5. ማዕረግ ምን ያህል ወደታች ልትሰጥም እንደምትችል ያሳይሃል::

ሁልጊዜ ከአንተ የቀደሙ ወይም ከአንተ በኋላ ያሉ ሰዎች መኖራቸውን ተረዳ፡፡

**6. ማዕረጎች ሊለወጡ የሚችሉ ናቸው ደግሞም በአብዛኛው ይለወጣሉ፡፡**

የአሁኑ ማዕረግህ የሕይወትህ ዘመን ሁሉ ደረጃ አለመሆኑን ስታውቅ ለወደፊቱ ለመሾም ተስፋ ይኖርሃል፡፡

**7. ወደ ቀጣዩ ማዕረግ ከመግባትህ በፊት እያንዳንዱ ማዕረግ በደንብ ሊታወቅ ይገባል፡፡**

እግዚአብሔር በመጋቢነት ደረጃ ላይ ካስቀመጠህ በደንብ መርምረህ አወቀው በመጋቢነት ሥራ ውስጥ ያለውን በሙሉ ድረስበት፡፡

**8. ከማዕረግ ወደ ማዕረግ መሾምን የሚወስኑ መርሆች አሉ፡፡**

ለምሳሌ፣ ባለህበት ማዕረግ ታማኝ እና ፍሬአማ መሆን ለሹመት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡

**9. ትክክለኛ የማዕረግ ለውጥ የሚመጣው እግዚአብሔር ራሱ ሲሾምህ ነው፡፡**

ዓመፀኞችን፦ አትበድሉ አልኋቸው፥ ኃጢአተኞችንም፦ ቀንዳችሁን አታንሡ

መዝሙር 75፡4

ሹመት ከእግዚአብሔር ነው የሚመጣው፡፡ በጌታ ያለኝ ሥፍራ በእግዚአብሔር የተሰጠ ነው፤ ያንተም እንዲሁ፡፡ እርስ በእርሳችን እንከባበር፤ እግዚአብሔርም ከፍ ወዳለ ማዕረግ ያሸጋግረናል፡፡

**10. ከፍ ወዳለ ማዕረግ ማደግ በአብዛኛው ከአዳዲስ ጥቃቶች ጋር ነው አብሮ የሚመጣው፡፡ አዲስ ደረጃዎች አዲስ ዲያቢሎሶችን ያመጣሉ፡፡**

የዳዊት ችግሮች የጀመሩት ጎልያድን ሲገድል ነው፡፡ ጎልያድን በመግደል ከአንድ ከማይታወቅ ወጣትነት ወደ ዕውቅ ጦረኛነት ማዕረግ ተሸጋገረ፡፡ ያኔ ነው ሳዖል ያየው እና ያሰቃየው የጀመረው፡፡

ከእግዚአብሔር የሆነ ሹመት ከስቃይ ጋር አብሮ ነው የሚመጣው፡፡ ከፍ ያለ ማዕረግ ያሉትን እንደምታዎች ማወቅ አለብህ፡፡ አሁን የለሁበት የአገልግሎት ደረጃ ላይ እግዚአብሔር ከፍ እንደሚያደርገኝ

በፍጹም አላውቅም ነበር። እንደዚህ ዓይነት ስቃይ እንደሚገጥመኝም በፍጹም አልጠበቅሁም።

> እሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።
>
> ማርቆስ 10፡30

## ምዕራፍ 123

# በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ወደተሻሉ ሰዎች ለውጣቸው

*ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና፥*

ፊልጵስዩስ 1፡19

ጥሩ መሪ ተከታዮቹን ይለውጣል። ተፅዕኖ የምታደርግባቸው ሰዎች መቼም አይረሱህም። ለዘለዓለም ባለውለታቸው ትሆናለህ። እግዚአብሔር መሪ እንድትሆን ከነገረህ ራስህን በምትመራቸው ሰዎች ሕይወት ላይ እየሰራህ ልታይ ይገባል። መሪነት ሊቀመንበር ወይም ፕሬዝዳንት ተብሎ መጠራት ብቻ አይደለም። መሪነት የሚያንጉ ማዕረጎችን መንበሽበሽ አይደለም። መምራት የተሻሉ ሰዎች እስኪሆኑ ድረስ ሰዎች ላይ መስራት ነው።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመራባቸው ሶስት ዓመታት ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ ተለውጧል።

*ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤*

የሐዋርያት ሥራ 4፡13

ጥሩ መሪ መሆን ሕይወትህን ለዘለዓለም ይለውጣል። ጥሩ መሪ በሕይወታቸው ሊረሳ እስከማይችል ድረስ የተከታዮቹን ሕይወት ይቀይራል። ጥሩ መሪ የእርሱ ዕዳ እንዳለባቸው እስከሚሰማቸው ድረስ የተከታዮቹን ሕይወት ይቀይራል። በጳውሎስና በፊልሞና መካከል የሆነው ይኸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳደረገ ፊልሞናን አስታውሶታል። ሕይወቱን እንኳን ሊሰጠው እንደሚገባው ነግሮታል።

*እኔ ጳውሎስ፡- እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር እንዳለብህ አልልህም።*

ፊልሞና 19

# የማይረሳ መሪ የመሆኛ ስምንት መንገዶች

## 1. አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ምራ

አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ስትመራ ወደ ጌታ ስላመጣኸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናል።

## 2. አንድን ሰው በመንፈስ ቅዱስ ወደ መሞላት ምራ

ዛሬ በምድር ላይ ወዳለው ወደ ታላቁ ኃይልና ረዳት ስለመራሃቸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናሉ።

## 3. አንድን ሰው በእግዚአብሔር ቃለ አፅና

ለሰው ልጆች ታላቁ የጥበብና የምሪት ምንጭ ወደሆነው ስለመራሃቸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናሉ። እኔ የጥሞናን ጊዜ እንዴት እንደማሳልፍ ላስተማረችኝ በጌታ እናቴ ለሆነችው ለዘለዓለም ባለዕዳ ነኝ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለኝ የየዕለት የጥሞና ጊዜ የሕይወቴ ታላቁ ምስጢር ሆኗል። በእርግጠኝነት ይህንን ታላቅ ምስጢር ላስተማረኝ ባለዕዳ ነኝ።

## 4. አንድን ሰው ወደ ትክክለኛው ቤተክርስቲያን ምራ።

ትክክለኛው ሕብረት በክርስቲያኖች መካከል ልዩነትን ያመጣል። አንድን ክርስቲያን ከድነት በኋላ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳይቆይ የሚያደርግ ምክንያት ነው።

## 5. አንድን ሰው ወደ አገልግሎት እንዲገባ እርዳ

አገልግሎት በምድር ላይ ያለ ከፍተኛ ጥሪ ነው። ለሰው ልጅ ከሁሉም ምርጥ የሆነ ሥራ ነው። ዘለዓለማዊ ዋጋ ያለው ብቸኛው ሥራ ይህ ነው። በአገልግሎት ውስጥ ለማገልገል ከመጠራት የሚልቅ ከፍ ያለ ልዩ ጥቅም እንደሌለ ሁላችንም መረዳታችን አይቀርም። የጊዜ ጉዳይ ነው።

## 6. አንድ ሰው እንዲያገባ እርዳው

ኢየሱስን ከመምረጥ በኋላ በሕይወት ከሚወሰኑ ታላላቅ ውሳኔዎች አንዱ የትዳር ጓደኛን ማግኘት ነው። ሊያጠፋህ ይችላል። አንድን ሰው ወደ ትክክለኛው ሰው በትክክለኛው ሰዓት እንዲያገባ ከረዳህ ሕይወቱን በሙሉ ባለውለታው ትሆናለህ።

## 7. የአንድ ሰው ጋብቻ እንዲተርፍ እርዳ

ጋብቻ እንደ ብርጭቆ ነው፣ በቀላሉ ይሰበራል። ችግር ውስጥ የገቡ ትዳሮች ለመፈወስ አስቸጋሪ ናቸው። የአንድን ሰው ትዳር ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲፈወስ ከረዳህ ሕይወቱን በሙሉ ያስታውስሃል።

## 8. በሕይወቱ ወይም በሕይወቷ አቋራጭ ላይ ትክክለኛ ውሳኔዎችን እንዲያደርግ/እንድታደርግ እርዳ።

ውሳኔዎች በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ትልቅ ልዩነት ያመጣሉ። ለምሳሌ የምትኖርበት ሥራህ፣ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ... አንድን ሰው በትክክለኛው አቅጣጫ እንዲሄድ ተፅዕኖ ካደረግህበት ለእርሱ የማትረሳ ሰው ትሆናለህ።

እኔ ጳውሎስ፦ እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር እንዳለብህ አልልህም።

ፊልሞና 19

*ምዕራፍ 124*

# ወደ ትክክለኛው ምድር በመሄድ ሽቅብ ውጣ

ብዙ ሰዎች ውድ የሆነውን ሕይወታቸውን ከአንድ ሥፍራ ወደሌላ በመወላወል ያባክናሉ። የምትኖርበት ቦታ ለስኬትህ በጣም ጠቃሚ ነው። ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር በየቦታው ሳይሆን *በአንድ ቦታ* ስለጠራህ ነው! ማንም በሁሉም ሥፍራ ስኬታማ አይደለም። ኢየሱስ እንኳን ሁሉም ቦታ አልተሳካለትም። ባልተፈለገበት በፍጹም አልቆየም። ኢየሱስ በየቦታው ኃይለኛ ተአምራትን ሊያደርግ እንዳልቻለ ይናገራል።

> ከዚያም ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት።... በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም።
>
> ማርቆስ 6፡1፣5

ደህና ተከታዮች በነበሩት ሥፍራ እንኳን ኢየሱስ የተለያዩ የስኬት ደረጃዎች ነበሩት። ብዙ ኃያል ሥራዎችን ሰርቷል፤ *አብዛኞቹ* የተከናወኑት ግን በተወሰኑ ከተሞች ነበር። በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የበለጠ ስኬት የታየባቸው መልክአ ምድራዊ ቦታዎች ነበሩ። ወደማታውቅባቸው ሥፍራዎችም ቢሆን እግዚአብሔር ከጠራህ ለመሄድ ፈቃደኛ ሁን። ሁላችንም የተላመድነውን አካባቢና የምቾት ክልሎቻችን እንወዳለን። ስለእርሱ ዓላማ በታዛዥነት ሥፍራህን በመቀየር ዝግጁ ስትሆን የእግዚአብሔር ሹመት እየተጠባበቀህ ነው።

> በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን ከተማዎች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ እንዲህም አለ፡-ወዮልሽ ኮራዚ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና...አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና።
>
> ማቴዎስ 11፡20፣21፣23

## በመሄዳቸው ስኬታማ የሆኑ ሰባት ሰዎች

**1. የተወለደበትን ሥፍራ ለቆ በመሄድ ዋና መስሪያ ቤቱን በቅፍርናሆም ባደረገ ጊዜ የኢየሱስ አገልግሎት አበበ።**

የተወለደበት ከተማ ያሉ ሰዎች ሊስብክ ተናደዱ።

እርሱ ግን እንዲህ አለው፦ አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤..ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው?

ሉቃስ 4፡16፤28

ይሁንና የቅፍርናሆም ሕዝቦች አገልግሎቱን ወደዱት። በቅፍርናናም ኢየሱስ አስተማረ፣ ሰበከ፣ እንዲሁም ብዙ ታላላቅ ሥራዎቹን አከናወነ።

ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።

ሉቃስ 4፡31፤32

የአገልግሎቴን ታላላቅ ተአምራት በአንዳንድ ሥፍራዎች አይቻለሁ። እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርግባቸው የተወሰኑ ቦታዎች እንዳሉት አውቃለሁ።

## 2. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ለመኖር በሄደ ጊዜ ስኬታማ ሆነ።

አንዳንዴ እግዚአብሔር እንድንሆን ወደሚፈልገን ሥፍራ ለመሄድ ፈቃደኞች አይደለንም።እንደ ዮሴፍ እኛም አንዳንዴ እስረኞች ሆነን መሄድ አለብን።

ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ ካወረዱት ከእስማኤላውያን እጅ ገዛው።

ዘፍጥረት 39፡1

## 3. ሩት ከሞአብ ወጥታ በኢየሩሳሌም ለመኖር ስትሄድ ስኬታማ ሆነች።

ሩትም። ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል

ሩት 1፡16

አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ሰዎች ሥፍራቸውን እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል። ሩት ባሏ የሞተባት ሴት ሆነች። ሕይወቷ መሪር አቅጣጫን ያዘ። እነዚህ ሁኔታዎች ራሳቸው ነበሩ ታዋቂ እንድትሆን ወደታየችበት ሥፍራ የሚመሯት። ሩት የንጉስ ዳዊት ቅድመ አያት ስለሆነች ወሳኝ ነበረች። በምድር ከኖሩ ሁሉ ባለጠጋ የነበረው የሰለሞን ቅም አያት ስለነበረችም ታዋቂ ነበረች።

## 4. ዳንኤል ከእየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ሲወሰድ ስኬታማ ሆነ

ለሶስት የተለያዩ አገዛዞች ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዲሆን ታይቶ ነበር። ዳንኤል በናቡከደነፆር መንግስት፣ ብልጣሶር መንግስትና በፐርሺያዊው ዳርዮስ ከፍተኛ ቢሮ ውስጥ አገልግሏል። ብዙ ከአፍሪካ የሄዱ የኢኮኖሚ ስደተኞች እግዚአብሔርን በማያምኑ በአውሮፓ አገር ውስጥ እንዲሰሩ እግዚአብሔር እየተጠቀመባቸው ነው።

## 5. ከአገሩ ወጥቶ ወደ ከነአን ሲገባ የአብርሃም ሕይወት ተሰወጠ።

*እግዚአብሔርም ታላላቆች እንበሪዎችን፥ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፥ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።*

ዘፍጥረት 12፡1

እግዚአብሔር አብርሃምን ከጣዖት አምላኪ ዘመዶቹ መነጠል ፈልጎ ነበር። አብርሃም መራቁ አስፈላጊ ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወትህ መከናወን ከመጀመሩ በፊት ሥፍራን መቀየር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

## 6. ከአጐቱ ከላባ ጋር ለመኖር ሲሄድ የያዕቆብ ሥራ አበበ

*ላባም። በዓይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ብሆንስ ከዚሁ ተቀመጥ እግዚአብሔር በአንተ ምክንያት እንደ ባረከኝ ተመልክቼአለሁና አለው።....ያ ሰውም እጅግ ባለ ጠጋ ሆነ ብዙም ከብት ሴቶችም ወንዶችም ባሪያዎች ግመሎችም አህዮችም ሆኑለት።*

ዘፍጥረት 30፡27፣43

## 7. እግዚአብሔር ከጠራው በኋላ ጳውሎስ በአሕዛብ መሐል ኖረ

የእርሱ አገልግሎት ለአህዛብ እንጂ ለአይሁድ አልነበረም፣ ይህንንም ያውቅ ነበር። እንደ ጠቢብ መሪ ስኬታማ የሚሆነው በአካል ትክክለኛው ቦታ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ከጅማሬው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መኖርን ተወ። ቀሪው ሕይወቱ በአሕዛብ መካከል ነበር። እንደመሪ ከጳውሎስ ስኬት ቁልፎች አንዱ ይህ ነበር።

*ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።*

ገላትያ 1፡15-16፣17

## ምዕራፍ 125

# የሥጋዊ ስሜቶችህን ተቆጣጠር

እግዚአብሔር በመላእክት አይደለም የሚሰራው፣ "ሥጋዊ ስሜቶች" ያላቸው ብዬ በምጠራቸው ወንዶችና ሴቶች ሰዎች ነው፡፡

ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤

2ኛ ቆሮንቶስ 4:7

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሸክላ ዕቃ የሚለው የሚያመለክተው ሥጋን ነው፡፡ ሌሎችን ለመቆጣጠር ከመሞከርህ በፊት ራስህን መቆጣጠር አለብህ፡፡ መሪ ለሥጋዊ ነገሮች ያለውን ተፈጥሯዊ ፍላጐት መቆጣጠርና መምራትናን መማር አለበት፡፡ ይህ ሥጋዊ ስሜት ካልተገታ አንድ ሰው ማንንም ሊመራ እንደማይችል ይደርስበታል፡፡ አንዳንድ ሰዎች መጾም አይችሉም፡፡ ሆዳቸውን መቆጣጠር አይችሉም፡፡ የተፈጥሮ ስሜቶችህ ተፈትተው ከተለቀቁ ጥሩ መሪ መሆን አትችልም፡፡

አንዳንድ ሴቶች የመቅናትና የመነጫነጭ ተፈጥሮአዊ ስሜት አላቸው፡፡ እነዚህን ሥጋዊ የተፈጥሮ ስሜቶች ካልገታሽ ማንንም መምራት አትችይም፡፡ ከቤተክርስቲያን አባላቱ (ከሚስቱ ሌላ) ልጆችን በተከታታይ ይወልድ የነበረን የቤተክርስቲያን መጋቢ አስታውሳለሁ፡፡ በቀላሉ የቤተክርስቲያኑ አባላት ማንም እስከማይቀር ድረስ እየተመናመኑ ሄዱ፡፡ መጋቢ ሥጋዊ የተፈጥሮ ስሜቶቹን በቁጥጥሩ ሥር አላደረገም ነበር፡፡

## ኢየሱስ የሥጋ የተፈጥሮአዊ ስሜቶቹን አሸንፏል

ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።

ዕብራውያን 4:15

ኢየሱስ በጌተሰማኔ የመናፈሻ ሥፍራ ሳለ የተፈጥሮ ሥጋዊ ስሜቶቹ ከመስቀሉ ሀሳብ እንዲያፈገፍግ አደረጉት፡፡ ይሁንና አጥብቆ ስለዚህ ነገር ፀለየ፤ እናም ራሱን መቆጣጠር ቻለ፡፡ ለአንተና ለእኔ ወደ መስቀል ሄደ፡፡ በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን የተፈጥሮ ስሜቶቹ

መላእክትን እንዲያድኑት መጣራትን እንዲያስብ አደረጉት። አሁንም ግን ራሱን ገታ።

መሪዎችን ከተከታዮች የሚለያቸው እነዚህን የተፈጥሮ ስሜቶች መቆጣጠር ነው። መሪዎች ምንም ስሜቶች፣ የሚፈትኑ ነገሮችና የሥጋ ምኞቶች የሌሏቸው አድርገህ አታስብ። እንደማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ስሜቶች አሏቸው።የመሪነት ቁልፉ እነዚህን ስሜቶችን በመቆጣጠር ነው። የተፈጥሮ ስሜቶቻችንን ብንከተል ኖሮ መቼም አንፀልይም፣ አንፆምም ወይም መጽሐፍ ቅዱሶቻችንን አናነብም ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ የተፈጥሮ ስሜቶቹን እንዴት እንደገታ ተናግሯል። ጳውሎስ ማድረግ ከቻለ እንግዲያውስ እኛም እንችላለን።

> ነገር ግን ለሌሎች ከሰበከሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።
>
> ፩ኛ ቆሮንቶስ 9፡27

## ምዕራፍ 126

# በሀሳባዊውና በእውነ መካከል ያለውን ልዩነት ተረዳ

ልምድ ያለው ሰው ከሀሳባዊውና በእውኑ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳውቅ ሰው ነው፡፡ "ሀሳባዊው" እንደሰማይ ከዋክብት ነው፡፡ የት መሄድ እንደምንፈልግ ይነግረናል፡፡ እውነታው "በምድር ላይ ያለው" ነው፡፡ በእርግጥ የት እንዳለን ያሳየናል፡፡ ንድፈ ሃሳቢዊ ዕውቀት ሃሳባዊውን ይነግርሃል፤ ልምምድ ግን እውን የሆነውን ይነግርሃል፡፡

ወጣትና ልምድ የሌላቸው ፖለቲከኞች በአብዛኛው ወደ ፖለቲካው ዓለም የሚገቡት ብዙ ዓይነት ሀሳባዊ ፍልስፍናዎችን ይዘው ነው፡፡ አብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች የኮሚኒስት እና ሶሻሊስት ዝንባሌ አላቸው፡፡ ከጊዜና ልምድ ሲመጡ ግን በአብዛኛው ነገሮች እንዳሰቡት ቀጥ ያሉ እንዳልሆኑ በአብዛኛው ያስተውላሉ፡፡ በአብዛኛው እንዲህ ዓይነት ሰዎዎችን ወደ ካፒታሊስት አስተሳሰብ ሲለውጡ ታገኛለህ፡፡

ሀሳባዊውና እውኑ በአገልግሎት ውስጥም ይታያሉ፡፡ የሆኑ ነገሮችን ብታደርግ የሆኑ ውጤቶችን እንደምታገኝ ልታስብ ትችላለህ፡፡ እየበሰልክ ስትሄድ ነገሩ እንደዚህ ቀላል አለመሆኑን ትደርስበታለህ፡፡ የቤተክርስቲያን ዕድገት መርሆች ቢተገበሩም ቤተክርስቲያኒቷ አሁንም አታድግም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ሀሳባዊው ከዕውኑ የተለየ ስለሆነ ነው፡፡ ልምድ ያንን ያስተምርሃል፡፡

ለሰባ ዓመታት ያህል መኖር ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢሆንም ገና ወጣት የሆኑ መጋቢዎች በዕድሜአቸው እጋማሽ ላይ ሳሉ ሲሞቱ አይቻለሁ፡፡ ሁሉም ሰው ቢፈወስ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው፡፡ ይሁንና እውነታው ይህ አይደለም፡፡ ኢየሱስ እንኳን ሁሉን ሰው ሊፈውስ አልሞከረም፡፡ ልምድ በሳል ያደርግሃል እንዲሁም የበለጠ እና ችሎታ ያለው መሪ ያደርግሃል፡፡

እየተማርክ ያለኸውን የብስለት ትምህርቶች አትናቅ፡፡ በልምምዶችህ ምክንያት የሥነ መለኮት አስተምሆሮዎችህን አትቀይር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል አሁንም እውነት ነው፡፡ እውነታው እኛ ሁሉን ነገር አለማወቃችን ነው፡፡ እውነታው ከሀሳባዊው በብዙ የሚለይበት ምክንያት አለ፡፡ በአብዛኛው እኛ ያልተገነዘብናቸው በሥራ ላይ ያሉ

ሌሎች ምክንያቶች አሉ። የምናውቀው ወይም የምንረዳው ሁሉን ነገር አይደለም። ጳውሎስ ሁሉን ነገር አልተረዳም። በድብዝዝ መስታወት እንደማየት አድርጐ ነው የገለፀው።

> ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡12

# ሀሳባዊነትና ከንቱ አስተሳሰቦች

መሪነት በአብዛኛው ብስለትን ይጠይቃል። ብስለት የሚመጣው ከልምድ ነው። የሕይወት ልምምድ ያጠነክርሃል። ለአመራር ብስለት ይፈለጋል። ብስለት ከንቱ አስተሳሰቦችንና ሀሳባዊነትን ያባርራል።

> በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡6

ዕጩ ፕሬዝዳንት ቢያንስ አርባ ዓመት ለምን መሆን እንዳለበት ጠይቀህ ታውቃለህ! በአርባ ዓመት ልምድ ከንቱ አስተሳሰቦችንና ሀሳባዊነትን ያስወግዳል። በሚያጠነክርህና የበለጠ ልምድ ያለው በሚያደርግህ መንገድ ተጓዝ። ከምታሳልፈው እያንዳንዱ ልምምድ ተማር።

ይህንን መጽሐፍ እየፃፍኩ የኬት ግሪንን መዝሙር እያደመጥሁ ነው። የእንደዚህ ዓይነት ሰው ዕድሜ ሃያ ስምንት ዓመት ላይ ለምን እንደሚቀጭ ሊገባኝ አይችልም። የእርሱ ዝማሬ ወኔ፣ ቅናት እና ቅባት ከዘቀጠው የዛሬ ቀን የክርስቲያን ዝማሬ ጋር ሊወዳደር አይችልም። ይሁንና ኬት ግሪን በዕድሜው አጋማሽ ላይ ተወስዷል። ሚስቱንና ትናንሽ ልጆቹን ለብቻቸው ተዋቸው። ለዚህ ማብራሪያ አለህ? እኔ የለኝም! ምስጢር የሆኑ ነገሮች ለጌታ ናቸው። በሳል ሁን!

> ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።
>
> ዘዳግም 29፡29

### ምዕራፍ 127

# በድርጅትህ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ዓይነት ሠራተኞች ለይተህ እውቅ።

በአንድ መሪ ሥር ሆነው የሚሰሩ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። ያሉትን ትክክለኛ ልዩነቶች መለየት ጠቃሚ ነው።

## ሁሉም መሪ መርምሮ ማወቅ የሚገባው አምስት ዓይነት ሠራተኞች

### 1. ከመስራት ይልቅ ማረፍን የሚመርጡ ሠራተኞች

እግዚአብሔር ለስድስት ቀናት ሠርቶ አንድ ቀን አረፈ። ይህም ከማረፍ መሥራት ይሻላል ማለት ነው። ከመሥራት ይልቅ ማረፍን የሚመርጥ ማንኛውም ሠራተኛ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሥራ አላገኘውም።

### 2. ምንም ተጨማሪ ወይም አዲስ ነገር ለመስራት ዝግጁ ያልሆኑ ሠራተኞች

እንዲህ ያሉ ሠራተኞች ዋጋ የላቸውም፣ ሁልጊዜ ሲሰሩ የነበሩትን ነው መስራት የሚፈልጉት። ለውጥን አይፈልጉም።

### 3. ማንኛውንም ሥራ ለመስራት ዝግጁ የሆኑ ሠራተኞች

እንዲህ ያሉ ሠራተኞች ጠቃሚ ናቸው። ለመማር ዝግጁ ናቸው። ለመሻሻል ይፈልጋሉ። ሊያስደስቱህ ይፈልጋሉ።

### 4. ውጤት - አምጪ ሠራተኞች

ከሠራተኛ ችሎታዎች ሁሉ ይበልጥ ጠቃሚ ከሆኑት መካከል አንዱ ውጤት የማምጣት ችሎታው ነው።

### 5. በሥራቸው የሚውሉና የሚዋጡ ሠራተኞች

ይህ ከፍተኛው የሠራተኛ ዓይነት ነው። ዋጋ ስጣቸው ከፍተኛ ክፍያም ክፍላቸው።

## ሁሉም መሪ ሠራተኛውን ማስተማር ያለበት ሰባት ነገሮች

1. ሁሉንም ሠራተኛህን አንተ ስትናገር መመሪያዎችን እንዲፅፉ አስተምራቸው
2. የተሰጣቸውን መመሪያ ደግመው እንዲናገሩት አድርግ፣ የሰጣሃቸውን መመሪያ በሚመለከትም ጥያቄዎችን ጠይቅ።
3. አዘውትረው እንዲደውሉልህ፣ እንዲያናግሩህና እንዲያማክሩህ አስተምራቸው።
4. ሥራቸውን ለመቀየርና አዳዲስ ኃላፊነቶችን ለመቀበል ዝግጁ እንዲሆኑ አስተምራቸው።
5. በሥራ ላይ በአግባቡ እንዲለብሱ አስተምራቸው።

እንደባንክ ያሉ ሀብታም ድርጅቶች ሠራተኞቻቸውን በጣም በሥርዓት እንዲለብሱ እንደሚያዝዟቸው አላስተዋልክም?

6. በሥራቸው ላይ የሚገጥሟቸውን ችግሮች መፍታት አስተምራቸው።

ችግሮችን ከማውራት ይልቅ ችግሮቹን እንዴት እንደፈቷቸው ማውራት አለባቸው!

7. በቤት ሳሉ ስለሥራቸው ማሳብን አስተምራቸው።

ስለሥራው በቤቱ ሳለ የሚያስብ ሰው በሥራው የተሳበና የተዋጠ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስለ ሥራቸው መጻሕፍትን ያነብባሉ። ገንዘባቸውንና ጊዜአቸውን ለሥራቸው በይበልጥ ለመዘጋጀት ይጠቀማሉ።

## በሥራህ እንዴት መዋጥ እንደሚቻል

1. ስኬታማ የምትሆነው ሙሉ ማንነትህን በዋጡ ነገሮች ብቻ መሆኑን እወቅ።
2. ስለ ሰዓት እንድታስብ የማያደርግህን ሥራ ፈልግ

   ይህ እግዚአብሔር የሰጠህ ሥራ ነው።
3. በቤትህም ሆነህ በሀሳብህ ሥራህን ቀጥል።
4. ስለሥራህ መጻሕፍትን ገዝተህ አንብብ

በድርጅትህ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ዓይነት ሠራተኞች ለይተህ እውቅ።

5. በአንተ ዓይነት ሥራ ውስጥ ያሉ ጓደኞች በብዛት ይኑሩህ።

ይህም የዕረፍት ሰዓቶችህ ሳይቀሩ ከሥራህ ጋር ተያያዥነት አላቸው ማለት ነው።

6. ለሥራህ የበለጠ የሰለጠነና የተዘጋጀ ለመሆን ገንዘብን አውጣ።

*ምዕራፍ 128*

# ሰዎችን በአንድነት የማቆየት ጥበብን አዳብር

## ሰዎችን በአንድነት የማቆያ አምስት ቁልፎች

1. **ሁሉንም ሰው በአንድነት ለማቆየት ጠንካራ ፍላጐት ይኑርህ፡፡ የአንድን ሰው እንኳ መጉደል ለማስቀረት ታገል፡፡ የኢየሱስ ዓላማ እግዚአብሔር ከሰጠው ሰዎች አንዱንም አለማጉደል ነበር፡፡**

መጋቢነት ሰዎችን በአንድነት የማቆየት ጥበብ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን የመከፋፈል አቅም ያላቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሰዎችን በአንድነት የማቆየትን ጥበብ ማዳበር አለብህ፡፡ ሰዎችን አንድ የማድረጊያው ቁልፍ ምንድን ነው? ሰዎች በአንድነት መሆን እንዳለባቸው በሚገባ ማመን አለብህ፡፡ *"ከፈለግህ ገደል ግባ"* ዓይነት አቋም ካለህ ከቡድንህ ብዙ ሰዎች ይጠፋሉ፡፡

## ሙሴ ሰዎችን በአንድነት አቆይቷል

> የሮቤልና የጋድ ልጆችም እጅግ ብዙ እንስሶች ነበሩአቸው አነሆም፥ የኢያዜር ምድርና የገለዓድ ምድር ለእንስሶች የተመቸ ስፍራ እንደ ነበረ ባዩ ጊዜ፥...እኛስ በአንተ ዘንድ ሞገስን አግኝተን እንደ ሆን ይህን ምድር ለባሪያዎችህ ርስት አድርገህ ስጠን ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን።....ሙሴም አላቸው። ይህንስ ነገር ብታደርጉ፥ ተዘጋጅታችሁም በእግዚአብሔር ፊት ወደ ሰልፍ ብትሄዱ፥እርሱም ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ ምድሪቱም በእግዚአብሔር ፊት ድል እስከትሆን ድረስ ከእናንተ ለው ሁሉ ጋሻ ጦሩን ይዞ በእግዚአብሔር ፊት ዮርዳኖስን ቢሻገር፥ከዚያ በኋላ ትመለሳላችሁ፥ በእግዚአብሔርም ፊት በእስራኤል ዘንድ ንጹሐን ትሆናላችሁ ይህች ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ርስት ትሆንላችኋለች።
>
> ዘኍልቁ 32፡1፤5፤20-22

ሙሴ አደገኛ ሁኔታ ገጠመው፡፡ የእስራኤል አንዳንድ ነገዶች የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር አልፈለጉም፡፡ ሣሩ ለከብቶቻቸው መልካም በነበረበት መቅረት ፈለጉ፤ ወዲያውኑም ጦርነት ሊነሳ ሆነ፡፡ እስካሁኑ ጊዜ በአንድ ላይ ነበሩ፤ አሁን ግን የእስራኤል ሕዝብ

ለሁለት ክፍሎች ሊከፈል ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን አንድ አድርጎ ለማቆየት የሚያስችል ጥበብ ለሙሴ ሰጠው።

ሙሴ እነዚያን ነገዶች ረግጦ ከፊስጉ ገሃነም እንዲገቡ ሊናገራቸው ይችል ነበር። የተረገሙ እንደሆኑ ሊነግራቸው ይችል ነበር። ይሁንና የሚናፍቁትን ምድር እንዲወርሱ እንዲሁም የእስራኤል አካል ሆነው እንዲቀጥሉ አስቻላቸው።

## 2. እግዚአብሔር የሚሰጥህን ሰዎች ሁሉ ውደድ

ሌላኛው ቁልፍ ሰዎችን ከልብ መንከባከብና መውደድ ነው። አንድን ሰው ከልብ ስትወደው በቀላሉ ልትለየው አትፈልግም። መሪ ለሰዎች እውነተኛ ፍቅር ሊኖረው ይገባል። ሰዎች ከልብ እንደሚወደዱ በሚያስቡበት ይቆያሉ። ተከታዮችህ የሚለያዩበት ምክንያት ቢኖራቸው እንኳን አንተ ለሁሉም ቡድኖች ያለህ ፍቅር በአንድ ላይ እንዲቆዩ ያደርገዋል።

## 3. አደገኛ ሁኔታዎችን ለመወጣት የእግዚአብሔርን ጥበብ ተጠቀም

በዚያን ጊዜም ሁለት ጋለሞቶች ሴቶች ወደ ንጉሡ መጥተው በፊቱ ቆሙ። አንደኛይቱም ሴት አለች። ጌታዬ ሆይ፥ እኔና ይህች ሴት በአንድ ቤት እንኖራለን እኔም ከእርስዋ ጋር በቤት ሳለሁ ወለድሁ።እኔ ከወለድሁ ከሦስት ቀን በኋላ ይህች ሴት ደግሞ ወለደች እኛ በቤት ውስጥ አብረን ነበርን፥ ከሁለታችንም በቀር ማንም በቤት ውስጥ አልነበረም።እርስዋም በላዩ ስለ ተኛችበት የዚህች ሴት ልጅ በሌሊት ሞተ። እርስዋም በእኩለ ሌሊት ተነሥታ፥ እኔ ባሪያህ ተኝቼ ሳለሁ፥ ልጄን ከአጠገቤ ወሰደች፥ በብብትዋም አደረገችው፥ የሞተውንም ልጅዋን በእኔ ብብት አደረገች። ልጄንም አጠባ ዘንድ በማለዳ ብነሣ፥ እነሆ፥ ሞቶ ነበር ነገር ግን ብርሃን በሆነ ጊዜ ተመለከትሁት፥ እነሆም፥ የወለድሁት ልጄ አልነበረም።ሁለተኛይቱም ሴት። ደኅነኛው የኔ ልጅ ነው፥ የሞተውም የአንቺ ልጅ ነው እንጂ አንቺ እንደምትዪው አይደለም አለች። ይህችም። የሞተው የአንቺ ልጅ ነው፥ ደኅነኛውም የእኔ ልጅ ነው አለች እንዲሁም በንጉሡ ፊት ይነጋገሩ ነበር።በዚያን ጊዜም ንጉሡ። ይህች። ደኅነኛው የእኔ ልጅ ነው፥ የሞተውም የአንቺ ልጅ ነው ትላለች ያችኛይቱም። አይደለም፥ የሞተው የአንቺ ልጅ ነው ደኅነኛውም የእኔ ልጅ ነው ትላለች አለ።ንጉሡም። ሰይፍ እምጡልኝ አለ ሰይፍም ይዘው ወደ ንጉሡ ፊት መጡ።ንጉሡም። ደኅነኛውን ሕፃን ለሁለት ከፍላችሁ ለአንዲቱ አንዱን ከፍል፥ ለሁለተኛይቱም ሁለተኛውን ከፍል ስጡ አለ። ደኅነኛውም የነበራት ሴት አንጀትዋ ስለ ልጅዋ ናፍቆአልና። ጌታዬ ሆይ፥ ደኅነኛውን ለእርስዋ ስጣት እንጂ አትግደል ብላ ለንጉሡ ተናገረች። ያችኛይቱ ግን፦ ይከፈል እንጂ ለእኔም ለአንቺም አይሁን አለች።ንጉሡም መልሶ፦ ይህችኛይቱ እናቱ ናትና ደኅነኛውን ሕፃን ለእርስዋ ስጡአት እንጂ አትግደሉት አለ።ንጉሡም የፈረደውን ፍርድ

እስራኤል ሁሉ ለሙ ፍርድን ለማድረግ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ ነበረበት አይተዋልና ንጉሡን ፈሩ።

1ኛ ነገሥት 3:16-28

ንጉሥ ስለሞን አደገኛ ሁኔታን ተጋፈጠ። በማን ወገን ነበር? ብዙ ጊዜ ሰወች መሪው ያህን ሰው ወይም ሌላኛውን ሰው ይደግፋል ማለት ይፈልጋሉ። በጋብቻ የማማከር ጊዜያት ላይ ብዙ ጊዜ በሚሰቶች ወይም በባሎች ወገን ነህ በሚል እወቀሳለሁ። ሰዎች በዚህ ወይም በዚያ ወገን ነህ ማለት ይፈልጋሉ። እንደዚህ ዓይነት አደገኛ ሁኔታዎችን መፍታት የእግዚአብሔርን ጥበብ ይጠይቃል። ጋብቻ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነገር ነው። በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ጥንዶች አብረው እንዲቀጥሉ የጋብቻ ችግሮችን በጥንቃቄ ፍታ። እውነተኛ መሪ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ነገሮችን የመፍታት ችሎታው እንዲፈታ ያደርጋል። ካልተሳካልህ፣ ሰዎችህ አብረው አይቆዩም።

## 4. በሰዎች መሐል ሰላም አስፍን

አብዛኞቹ የዚህ ዓለም መሪዎች ግጭቶችን በማብረድ የተጠመዱ ናቸው። እውነታው የሰው ልጆች ያለማቋረጥ ሰላም ሊኖር እስከማይችል ድረስ እጅ ብዙ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች አሏቸው። መሪ የሆነ ሰው ሁሉ ሰላም የማስፈንን ጥበብ መማር ያስፈልገዋል።

ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።

ዕብራውያን 12:14

ብዙ ፕሬዝዳንቶች በጦረኛ አንጃዎች መካከል ሰላም የሚያውርዱት እነርሱ መሆን እንደሚመኙ አላስተዋልክም? ተከታታይ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች በመሐከለኛው ምስራቅ ሰላም የሚያወርዱት እነርሱ እንዲሆኑ ናፍቀዋል። በማይታረቁ ጥለኞች መሐከል ቆመው ፎቶ ይነሳሉ። እነዚህ ፎቶግራፎች ስለመምራት ችሎታቸው ሰስሚመሰክሩ ይጠቅሟቸዋል። ስዚህም ዓለም ሰላም ማምጣት የሚችል ማንኛውም ሰው የመሪነት ችሎታዎች አሉት።

መሪ ነህ? በጠላቶች መሐል ሰላም እንዲመጣ ትተባበራለህ? ወይስ ጥላቻንና ሁከትን ታባብሳለህን? መሪ ሰላምን እንጂ የበለጠ አለመግባባትን አያመጣም።

## 5. ከሌሎች ጋር ሰላም ይኑርህ

አንዳንድ ሰዎች ያለማቋረጥ በጦርነት ላይ ናቸው። ከሚያጋጥማቸው ሰው ጋር ሁሉ ጭቅጭቅ ይፈጥራሉ ማለት ይቻላል። ከቤተ ክርስቲያናቸው ብዙ ሰዎችን ያሸሹ አንዳንድ የመጋቢ ሚስቶችን አውቃለሁ። ያለማቋረጥ የምትጣላቸውን ሰዎች መምራት አትችልም። ለምን ማንም እንዳማይከተልህ ገርሞህ ይሆናል። ደግሞ ከጀርባ የሚወጋቸውን ሰው እንዴት ሊከተሉ ይችላሉ? በየደቂቃው እየዞረ ድንጋይ የሚወረውርብህን ሰው ትከተላለህ? በፍጹም!

መሪ መሆን ትመኛለህ? በዙሪያህ ካሉት ጋር በሰላም የመሆንን ጥበብ አዳብር። ያለማቋረጥ አትዛትባቸው። በእርግማኖች አታስፈራራቸው።

አንዴ ከአንድ የእግዚአብሔር ሰው ጋር ለመነብኘት ተጋበዝኩ። መሄድ አልፈለግሁም። ሰዎችን ብዙ ጊዜ ሲረግም ያንን ሰውዬ አይቸዋለሁ። በሀሳቤ "ምናልባት ዛሬ እኔን ይረግመኛል" አልኩኝ። ትንሽ ሳይከብደው የሚራገም ሰው አጠገብ መሆን አልፈልግም።

የመሪነት ጥበብ በዙሪያህ ካሉት ጋር በሰላም የመሆን ጥበብ ነው። በሌሎች ስኬት አትረበሽ። አንተ የሌለህ የሆነ ነገር ስላላቸው አትዋጋቸው። ኑሮዬ ይበቃኛል በል። የሌሎች ሰዎችን ስኬት ተቀበል። ደግሞም አትዋጋቸው።

ከሌሎች ጋር በሰላም የመሆን ቁልፍ ምንድን ነው? እንደማንነታቸው ተቀበላቸው። በዙሪያህ ያለውን ሰው ሁሉ ለመለወጥ አትሞክር። እኛ ሰዎች ብቻ ነን ስህተቶችም አሉብን።

*ምዕራፍ 129*

# ስለምተጠየቅበት ቀን ያለማቋረጥ አስብ

እያንዳንዱ መሪ እያደረገ ወይም እያደረገ/ች ስላለው/ችው ነገር ይጠየቃል፡፡ ስለሰጠህ በጐች ለእግዚአብሔር መልስ ለመስጠት ዝግጁ ነህ? ኢየሱስ ከጥፋት በስተቀር እግዚአብሔር ከሰጠው በጎች አንዱንም እንዳላጐደለ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ ጳውሎስም መልስ መስጠት እንደሚኖርበት ይናገር ነበር፡፡ እነዚህ ያለማቋረጥ ስለሚጠየቁበት ቀን የሚያስቡ መሪዎች ነበሩ፡፡

> ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።
>
> ዕብራውያን 13፡17

መሪነት ትልቅ ኃላፊነት ነው፡፡ ከዓመታት በፊት ብዙ የጋና ሀገር መሪዎችና ሚኒስቴሮች በተኲሽ ጓዶች ሲረሸኑ እንደተመለከትኩ አስታውሳለሁ፡፡ ወሳኝ ሰዎች ሲዋረዱና ሲገደሉ ማየት አሳዛኝ ነበር፡፡ ብዙ ተራ ዜጐች እንደዚህ ዓይነት ነገር አልደረሰባቸውም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙ ተራ ሰዎች አገሪቱን የመምራትን ኃላፊነት ስላልወሰዱ ነው፡፡ ይሁንና የመሪነትን ኃላፊነት የወሰዱት በሕይወታቸው መክፈል ነበረባቸው፡፡

ለአመራርህ መልስ እንደምትሰጥ ያለማቋረጥ የምታስታውስ ከሆነ የተሻለ መሪ ትሆናለህ፡፡ የምትጠየቅበት ቀን እየመጣ እንደሆነ ሁልጊዜ አስታውስ፡፡ ይህ ትክክለኛውን ነገር እንድታደርግ ያደርግሃል፡፡ ስለ አገልግሎቴ ለእግዚአብሔር መልስ እንደምሰጥ ያለማቋረጥ አሰላስላለሁ፡፡ በአብያተ ክርስቲያኖቼ ላሉ አባላት መልስ መስጠት እንደሚኖርብኝ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው እነርሱን ለመጠበቅ ትልቅ ጥረት የማደርገው፡፡

መሪ ነህ? ያለማቋረጥ ስለምትጠየቅበት ቀን እያሰብክ ነው? እባክህ አስብ! የላቀው የውስጥ መነሳሳት ቁልፍ ይህ ነው፡፡

# በዳግ ሂዋርድ-ሚልስ የተጻፉ ሌሎች መጽሐፍት

## የታማኝነትና ታማኝ አለመሆን ርዕሶች

- አባቶች እና ታማኝነት
- መሪዎችና ታማኝነት
- ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን
- የሚወነጅሉህ
- ዝንጉዎች
- ትተውህ የሚሄዱ
- አስመሳዮች

## የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ርዕሶች

- የቤተ ክርስቲያን እድገት
- ቤተ ክርስቲያን መትከል
- ሜጋ ቤተ ክርስቲያን(2ኛ እትም)

## የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ርዕሶች

- ቅባቱን ያዝ
- በምልክቶች እና በድንቆች ማገልገል
- ወደ ቅባቱ የሚያደርሱ እርምጃዎች

## የስኬት ርዕሶች

- አሥራት የማይከፍሉ ክርስቲያኖች ለምን ይደኸያሉ . . . እና አሥራት የሚከፍሉ ክርስቲያኖች እንዴት ሀብታም እንደሚሆኑ

## የመጋቢነት አገልግሎት ርዕሶች

- የአመራር ጥበብ 2ኛ እትም
- የእረኝነት ጥበብ
- የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ

## የክርስቲያን ሕይወት ርዕሶች

- ወደኃላ ማፈግፈግ
- የጋብቻ ሞዴል
- ልጄ ሆይ፣ ትችያለሽ
- አጋንንቶች እና እንዴት እነርሱን ማሸነፍ እንደሚቻል
- ሰይመው! ይገባኛል በል! ውሰደው!
- የጥሞና ጊዜ
- ንገራቸው! .

## የአገልግሎት ሥራ ርዕሶች

- በእግዚአብሔር ፍጹም ፍቃድ ውስጥ መሆን እንዴት እንደሚቻል
- ማጣት፣ መከራ መቀበል፣ መሥዋዕት መሆን፣ መሞት
- የተጠሩ ብዙዎች ናቸው
- ፕሩቶን
- የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሕግጋት
- የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሕግጋት

# የመሪነት ጥበብ

ሁለተኛ እትም

ለአገልግሎት መጠራት ለመሪነት መጠራት ነው፡፡ በድጋሚ፣ በቀላሉ በቀረበና ሊተገበር በሚችል አቀራረብ ዶክተር ሂዋርድ ሚልስ ልዩ ክርስቲያን መሪ ያደረጉትን መርሆች ያብራራል፡፡ በዚህ የተገለጠው እውነት ብዙዎችን ለመሪነት ጥበብ ያነሳሳል፡፡

## ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

በርካታ ተፈላጊ መጽሐፍ የጻፉና ከእነዚሁም ውስጥ "ታማኝነትና ታማኝ አለመሆን"የተባለው በአለም ላይ ታዋቂ በሆነውን መጽሐፋቸው ሲታወቁ፣ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ "የላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል"ዓለምአቀፋዊ ዲኖምኔሽን ቤተ ክርስቲያን መስራች ናቸው፡፡

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ፣ በአለማቀፍ ደረጃ ወንጌላዊ ሲሆኑ "ፈዋሹ ኢየሱስ ክሩሴድ (HEALING JESUS CRUSADE) " በተሰኘው እና በአለም ዙሪያ በተያዩ ኮንፈረንሶች ላይ በአገልግሎታቸው ይታወቃሉ፡፡ይበልጥ መረጃ ከፈለጉ ዌብሳይታቸውን ይጎብኙ፣ www.daghewardmills.org.

The Art of Leadership

Second Edition

ሮኖቦት ኢታሚዎች